# እስቲ የነበርነው እንጻፍ!

## የኢ.ሕአፓ ረጅም ትግል

ኢ.ያሱ ዓለማየሁ

የኢ.ሕአፓ የ41 ዓመት መራራና ረጅም ትግል ረጅም ትዕግስትን ጠይቋል። አያሌ ፈተናዎችን ተቋቁሞና አልፎ ዛሬም ህልውናውን ጠብቆ በትግሉ ሜዳ ላይ መገኘቱ በቅድሚያ የአባላቱ -- ታሪክን ገርተውና ጽፈዋት ያለፉትም ሆነ በሕይወት ያሉትን ጽናትና ቆራጥነት- የሚመለከት ነው። ኢ.ሕአፓን ለመመስረትና መስርቶም ለማታገል በተደረገው ትግል በታሪክ አጋጣሚ ዋና ተካፋይ ሆኜ በመቆየቱ የሚሰማኝ ደስታና ክብርም ወደር የለውም። ሀቁ ይህ ድርጅት ከቶም ባልተመሰረተ የሚሉት ጠላቶች እንደነበሩትና እንዳሉት ሁሉ (በአብዛኛው ከስርዓቶቹ ጋር የተያያዙ) ቤዛችን ነው፡ የወኔያችን መከሰቻ ነው፤ የሀገር አለኝታችን ነው፤ ድርጅታችን ነው የሚሉ ደሞ ብዙዎች ናቸው።

ስለ ተማሪው እንቅስቃሴም ሊተቹ የተነሱ ብዙዎች በ እንቃስቅሴው ያልተሳተፉና ውስጡንም የማያውቁ መሆናቸው የታዘብነው ነው። መሬት ለአራሹ ብለው ታላቆቻችን በተሰለፉ ቀጣይ ዓመት ወደ ዩኒቨርስቲ የገባነው ሁሉ እነ ሃይሉ ገሞራውን፤ ብርሀነ መስቀልን ወዘተ ማድነቃችን የግድ ነበር። የተማሪው እንቅሳቃሴ ወደ ግራ ያዘነበለው የነበረው አማራጭ ስር ነቀል ለውጥ የሚል ሆኖ በመገኘቱ፤ የንጉሱ፤ የአፓርቴይድና የቅኝ ገዢዎች ደጋፊ አሜሪካን ተቃርነው የቆሙት የሶሻሊስት ሀገሮች በመሆናቸውም ነበር። በዓለም አቀፍ ደረጃም የነጻነት እንቅስቃሴዎች -- በአብዛኛው ግራ ክንፎች -- ከቬየትናም እስከ ደቡብ አሜሪካና አፍሪካ ይካሄዱም ነበር -- ማለትም የፋኖ ተሰማራ፤ የነ ቼና ሆ ቺ ሚንህ ጊዜ ነበር። በሀገር ውስጥም ደግሞ ጸረ ባንዳ የነበሩት እነደጃዝማች ታከለና ሌሎችም በአለው አገዛዝ የተበደሉ አርበኞች ምሳሌዎች ነበሩ። ካርል ማርክስ ሲጽፍ ናፖሊዮን የጨው ግብር ሲያውጅ ግዕሙን አጣ እንዳለው ሁሉ ንጉሱም እነ መንግስቱ ንዋይን ሲሰቅሉ ክብራቸውን ገፈው ጣሉ ማለት ይቻላል። በአጭሩ ወደ ግራ የፖለቲካ

መስመርና ወደ ሶሻሊዝም ማዘንበላችን የሚጠበቅ ነበር። በዩኒቨርሲቲውም ያቋቋምነውን ሁሉን አቀፍ የአዲስ አበባ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ማህበርና ብሔራዊ ማህበር ለመቃወም በዩኒቨርስቲው ፈረንጅ አስተማሪዎችና አስተዳደር ስር የተቋቋሙት "የዱሮውን መላሽ" (ሬስቶረርስ) ደግሞ ብዙሃኑን ተማሪ አሳምነው የበላይነትን ሊያገኙ አልቻሉም። ሁሉን አቀፍ ማህበር በመቋቋሙ ግን የተማሪዎ ትግል በተቀነባበረ መልክ ሊካሄድም ቻለ። ስርዓቱ ለለውጥ ክፍት ባለመሆኑና አፋኝና ኋላቀርም ስለነበር ከአመት አመት ተማሪው ሲሰለፍና ሲጠቃ ይበልጥ እያመረረና እየከረረም መጣ። ተማሪዎች ከመደብደብ ሌላ፤ በአስለቃሽ ጋዝ ከመጠቃት ሌላ መገደልም ጀመሩ። በግጥሙም ሆነ በተግባር የቆራጥነት ምሳሌ የነበረን ሀይሉ ገብረ ዮሐንስ (ገሞራው) ነጋ ጠባ እየተያዘ አስቃቂ ስየል ተፈጽሞበታል። ዝርዝር ታሪኩን ኢሕአፓ ታሪኩን ሲጽፍ ያቀርበዋል በሚል ልተወውና ወደ ፓርቲ ምስረታው ሂደት ላምራ።

የተማሪው እንቅስቃሴ ሚናው የፓርቲ ሊሆን አለመቻሉን ሁኔታው ሲገልጽ ድርጅት ማቋቋም አለብን የሚለው እምነት እየጠነከረ በመምጣቱ ይህን ለማድረግ መዘጋጀት አለብን የሚል ስሜት አየለ። ዋለልኝ መኮንን "ለአዋጅ አዋጅ" ብሎ ከጻፈ በኋላ አጼውን ባልተለመደ ደረጃ የሚያጋልጥ ወረቀት ለማውጣት እኔ፤ ብንያም አዳነና ዛሬ በአዲስ አበባ ያለው አ. ገ. ኢ. በብንያም ቤትና በእኔም ቤት ተገናኝተን "እንኳን ለ 77ኛው የደም ልደትዎ አደረሶት" የሚልና ንጉሱን በጠነከረ ደረጃ የሚያጋልጥ ወረቀት ጽፈን ተበተነ። የ ሶስታችን ግንኙነት በዚሁ ተጠናከረና (ብንያምና እኔ ጓደኞች ነበርን) በውይይት መሃል ድርጅት ማቋቋም እንዴት የሚለው ተነስቶ ድርጅት የሚመራው የታጠቀ ሀይል መኖሩም አስፈላጊነቱ ታምኖበት (ስራዓቱን በሰላም መቀየር የሚል ሀሳብ ከቶም አልነበረምና/አይቻልም ነበረና) ወደ ውጭ ሀገር ሂዶ፤ በውጭ ካሉ ታጋዮች ጋር ተገናኝቶ፤ ድርጅት መስርቶ፤ ወታደራዊ ስልጠና ወስዶ፣ ወደ ትግሉ ሜዳ መመለስ የሚል ሀሳብ ቀረበ። ከዚህ ተያይዞ ነው እንግዲህ ትግሉን ለማስተዋወቅ ሊረዳ ስለሚችል አይሮፕላን መጥለፍ የሚለው ሀሳብ መጥቶ ሌሎችንም መመልመል ያስፈልጋል በሚል ስምሪት የተጀመረው። የምናምናቸውንና እነሱም የሚያምኗቸውን ጓዶች ቀርበን ስለ ዕቅዱ ስናካፍላቸው ብዙዎቹ "እሽ" ሲሉን "አይ አይሆንልንም" ያሉንም ነበሩ። ግን የሚያጋልጡን ከቶም አልነበሩም -- አላጋለጡንም። ለጥቆ ያለው ትረካ በዚህና ዛሬ

የሚቀርብ አይደለም። ለማንኛውም ጠለፋው ተሳክቶ ሱዳን ደርሰን በሱዳን ስንታሰርና የነበረው ሁኔታ ራሱን የቻለ ታሪክ ነው። በዚህ ቦታ መጥተው የጠየቁን አንድ ስደተኛ ኢትዮጵያዊና (በደርግ ጊዜ ከስደት ተመልሰው ያረፉና) ኪዳኔ የሚባል የጀብሓ አባል (በራሱ ድርጅት የተገደለ) ብቻ ነበሩ። ታሪክ ለማሳጠር እኛ ከሱዳን አንወጣም ስንል ሱዳን ደግሞ ከንጉሱ በኩል ተጽዕኖ ስለነበረበት ውጡ የሚል አምጥቶ ጭቅጭቅ ተጀመረ። ምስራቅ ጀርመን ሂዱ አሉን እምቢ አልን። ሶቪየት ሕብረት ሂዱ፡ ቻይና ሂዱ አሉን አይሆንም አልናቸው። መቆየት ምንፈልገው ሱዳን መሆኑን ገለጽንላቸው። የወቅቱ ባለስልጣኖች -- ከጊዜ በኋላ ኒሜሪ የሚገድላቸው -- ተመላልሰው ቢያነጋግሩንም እሺ ብለን ወደ ምስራቅ አውሮጳ ወይ ቻይና አልሄድንም። በካርቱም ይደረግ ለነበር የአፍሪካ ስብሰባ ጃንሆይ አልገኝም ስላሉም ሱዳን እኛን መመለሱን ስላልፈቀደ በጸጥታ ሰራተኞቹ አጅቦ ወደ ካይሮ ሰዶን፣ ከዚያም የግብጽ የጸጥታ ሰራተኞች ተረክበውን ልንሄድ ወደአልፈለግንበት አልጀሪያ አደረሱን። ይህም ጊዜውን የሚጠብቅ ሌላ ዝርዝር ታሪክ አለው።

ይህን ማንሳት የተገደድኩት አውቅን ብለው መጽሃፍ የጻፉ ድርጅቱን የምዕራብ ጀርመንና አልጀሪያ፣ የኤርትራው ሳቤ ወይም ሌላ አቋቁመው የሚሉት ጭራሽ ሀሰት መሆኑንም ለመግለጽ ነው። ድርጅቱ የተመሰረተው ለውጥ እናመጣለን ባሉ ወጣት ኢትዮጵያውያን ነው። ከኤርትራም ሆኑ ሌሎች ግንባሮች በቅጡ ግንኙነት ለማድፈግ የተሞከረው ድርጅቱ ከተመሰረተም በኋላ ነው። ስለዚህም ድርጅቱ በሻዕብያ ሆነ በሌላ ተመሰረተ የሚባለው ጭራሽ ሀሰት ነው። የኤርትራ ግንባሮችን በተመለከተ የነበረው ሁኔታና ተመክሮ ታሪክ እስከሚዘግበው ጊዜውን ጠባቂ ነው። ያም ሆነ ይህ ግን ዞረን አልጄሪያ ገብተን ብዙ መከራ ብናይም የድርጅቱን ምስረታ ግዳጅ በመቀጠል ሀገር ቤት ካሉን ከእስር ከተፈቱ ጓዶች ጋር (ጸጋዬ ደብተራው፣ ዋለልኝ፣ ጸሎተ ሕዝቅያስ ወዘተ) ጋር ግንኙነት በመቀጠል ጥረቱ ተጧጠፈ። በአሜሪካ መስፍን ሐብቱ የዚሁ የምስረታ ምልመላ ጥረት ዋና አካሂያጅ ሆኖ ሳለና አልጀሪያም ድረስ መጥቶ በሰፊው ከተወያየን በኋላ ራሱን ገደለ በመባሉ ጥረታችን እንቅፋት አጋጠመው። ሆኖም የሚቋረጥ አልነበረምና ቀጠለ። ቆይተው መኢሶን የሚሆኑትንም ለማግባባት ተጥሮ ሚቹ ሀይሌ ፊዳም ወደ አልጄርስ መጥቶ ሁሉ ውይይት ተካሂዶ ነበር። ስምምነት ግን መድረስ አልተቻለም። ደርግም አድብቶ ተለጣፊ

ያላቸውንም ፈጅቷል። ድርጅታችን መኢሶን ከሆኑት ጋርም የቆየ የፖልቲካ አቋዋም ልዩነት ቢኖረውም (ሀይሌ ፊዳ አልጀሪያ መጥቶ ብንወያይም ልንፈታው ያልቻልነው ልዩነት) በአዲስ አበባ ተስፋዬ ደበሳይ (ድርጅታችንን ወክሎ) ሀይለ ፊዳም ድርጅቱን ወክሎ ውይይቶች ተካሂደው  መኢሶን "ሂሳዊ ድጋፍ የሚለውን" ድርጅታችን ባለመቀቡ መስማማት አልተቻለም። ሆኖም ግን ሁለታችንም በያዝነው ልንቀጥል ግን ላንጎዳዳ ተብሎ የነበረውን አፍርሰው ለቀጣዩ ሽብር መንገድ ከፋችና ተባባሪ ሆነዋል። የደርጉ አጫፋሪዎች ዛሬ ደርግ ሀላፊነት የለውም የተዋጉት ሁለት ኡ ድርጅቶች እርስ በርሳቸው ነው የሚለውን ልብወለድ አረመኔው መንግስቱ  ቢደጋግመውም ጸያፍ ልብወለድ ነው።

ኢሕአፓ በረጅም የትግል ታሪኩ ብዙ ውጣ ውረድ ተፈታትኖታል። ይህ ደግሞ የሚጠበቅ ነው -- ትግል የፎገራ ሜዳ አይደለምና። በበኩሌ የድርጅቱን ብርታት እና ጽናት የማከብረው በድሉ ብቻ ሳይሆን ቀውስና ችግር ሲመጣበት ሊወጣ በመቻሉ ነው። በ ድርጅቱ ታሪክ የመጀመሪያው ችግሩ ምስረታውን እውን ለማድረግ ያደረገው ትግል ነው። የወቅቱን ሁኔታ የማያውቁ ያኔ በ1964 ሁሉም ለትግልና ለመደራጀት ዝግጁ የነበረ ይመስላቸዋል -- ሀቁ ግን ይህ አልነበረም። ወጣቱን ከትግል ለማራቅ አሜሪካና ስርዓቱ ታግለው ብዙዎች ፓርቲ ሲባሉ ጭፈራ ይመስላቸው ነበር።  ይህን ችግር የየካቲት አብዮት አስወግዶ ወጣቱ በብዛት ተስተካክሎ በሀገራዊው ትግል ተካፋይ ሆኖም መስዋዕትነትን ከፍሏል። ድርጅቱ ከተመሰረተና ትግሉን ማፋፋምም ሲይዝ ሌላው ችግሩ ቀይ ሽብር የተባለው አረመኔ ጭፍጭፋ ነበር። ይህን ግፍ ድጋፊና ኣጋዥ ሆነው የመጡት የብርሃነ መስቀል አንጃዎች ደግሞ ሌላ ድርጅቱ ላይ የመጡበት አጥፊ አንበጣዎች ነበሩ። የነ ብርሀነ መስቀል ጌታቸው ማሩ አንጃ ድርጅቱን ይህ ነው በማይባል ደረጃ ቢጎዳም ድርጅቱ ይህንንም ተቋቁሞ ትግሉን ለመቀጠል መቻሉ ትልቅ ድል ሆኖ ይገኛል። ቀጣይ አንጃዎችም -- እስከዛሬም ቢሆን-- የመጀመሪያውን ጎዳናና ጫጫታ ተከትለው ድርጅቱን ሊጎዱና ሊያጠፉ ቢጥሩም ድርጅቱ ተቋቁሞአቸው ህልውናውን ጠብቆ አለ። በዚህ ሁሉ ትግል ተሳትፌ አንጃን ወያኔ እንደሚለው በማምከን ወይም እኛ እንደምለው ከጥቅም ውጪ በማድረግ ከጓዶች ጋር ሆኜ በመሳተፌ ደስታ ይሰማኛል። አንጃነት፤ ብተና፤ አንጃነት፤ ክህደት ወዘት አገዛዞች ካደረሱብን ጉዳት ያላነሰ ጥቃት አድርሰውብናል። ግን እነሱ ከሰሙ እንጂ ድርጅታችን ከቁስሉ አገግሞ አለና እንዳለ ነው። ለምንና እንዴት

ስንል ደግሞ የአባላቱን ጽናትና የመስመሩን ትክክለኛነት የሚጠቁም ነው። ይህ ደግሞ የተወሰኑ መሪዎች ስራ ሳይሆን መላ አባላቱ ህዝባዊ ቃል ኪዳኑን አክብሮ መገኘቱን የሚመለከት ነው ብየ አምናለሁ።

ከወያኔ ጊዜ ወዲህ በርካታ መጽሃፍት -- ስለ ኢሕአፓ ሳይሆን-- በድርጅቱ ላይ ተጽፈዋል። ለማውገዝና የሀሰት ዘመቻ ለማድረግ። የነበርነውና እናውቃለን የምንለው እነዚህ ወያኔ የሚያዳንቃቸውን ስናነብ ንዴት ሳይሆን የሚመጣብን ሳቅ ነው። በግሌ ደረጃ ኤርትራዊ መሆኔ፤ ብዙ ሚሊዮን ከድርጅቱ ዘርፌ የምንደላቀቅ መሆኔ፤ ጓዴን ጸጋዬ ደብተራውን ለወያኔ አትልቀቂት ብዬ መምከሬን፡ ወዘተ ወዘተ። አንዱ ኣውቃለሁ ባይ የደርግ አረመኔ ባሳተመው መጽሃፍ በአዲስ ኣበባ ተገኝቼ ያውም ከመኢሶን ዋና ካድሬ ጋር መንግስቱ ይገደል ብዬ ማጽደቄን ሁሉ ጽፏል። ከእኔ በላይ -- ማለትም ግለሰብ ነኝና -- ድርጅቱንም ሀገር ሸጠ፤ አስገነጠለ፤ ለሻዕቢያ አገዘ፤ ከሶማሊያ ጎን ተሰለፈ፤ ወዘተ በሚል አያሌ የሀሰት ክሶች ወርደውበት ዛሬ የሀገሩን ታሪክ ለማወቅ የማይጥር ትውልድ አባሎች ይህንኑ እንደ አቡነ ሰማያት ሲደግሙ እያዳመጥን ነው። ሀቁ ይነገር ከተባለ ግን፤

- ወያኔ ትግሌ ለመገንጠል ነው ብሎ ሲነሳ ማን ተቃወመው ታገለው?
- ሻዕቢያ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ሲል ማን አሌ አለው?
- ወያኔ በባዕዳን ድጋፍ ለስልጣን ሲበቃ ማን ታገለው? ማን ግን ተኮለኮለለት?
- ሲሶ ኢትዮጵያን የምዕራብ ሶማሊያ አካል ነው ብሎ ማን ሞቃዲሾ ፈረመና ተጠቀመ? ማንስ አሻፈረኝ አለ?
- ማን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለዘመናዊ ባርነት አሳልፎ ሸጠ?
- ማን ግንጠላን ደገፈና ሀገርን ጎዳ?
- ማን ሕዝብን ከፋፋለ?
- ወዘተ ወዘተ

መሰረታዊ ጥያቄዎች ሲነሱ መልሱ በጣም ግልጽ ነው።

ታሪክን መፋቅ ግን ልምዳቸው የሆነ የሚሉትን ነጋ ጠባ ማስተባበሉን ባንፈልግም በተቻለ መጠን ግን በየጊዜው ምላሽ መስጠታችን አልቀረም። በበኩላችን ብዙውን ጊዜ በዝምታ

የምናልፌው ሀቁና መልስ ጠፍቶን ሳይሆን ወደ ዋናው ጠላት ላይ ብናተኩር ይበጃል በሚል ነው። ዛሬ ባለንበት ሁኔታ ደግሞ ሀቁን ማቅረቡና እገሌን እገሌ ማለቱ አይጠቅምም ብለን ዝምታን መርጠናል። በበኩሌ በትግልና በኢሕአፓነት ያሳለፍኩት ረጅም አመታት ብዙ ምስጢሮችንም የማወቅ እድል ሰጥቶኛል -- ድርጅቱ ይባል ይነገር ሲል ሁላችንም የምንናገረው ይሆናል። የምናውቀው ሳንናገር የማያውቁት እየተንጫጩ ታሪክን ሊበርዙ እየጣሩ ናቸው። የሚያስገምታቸው ደግሞ ድርጅቱ ይህን ሁሉ አመት መታገሉን እንደ ጥፋት ቆጥረው መለፈፋቸው ነው። ጸጋ ነው ያኮራናል በማለት ፈንታ። ቀጥለውም በማያገባቸው ገብተው መሪዎች ባጁ፣ 40 አመት አለፋቸው ወዘተ ብለውም ይዘልፋሉ። በመጀመሪያ ደረጃ አባላት ከመረጧቸው 40 ቀርቶ -- ከቻሉና ብቁ ከሆኑ -- ከዚያም በላይ በአመራር ሊቆዩ ይችላሉ። እንደምናውቀው ግን ሁሉም አንጃዎች ዓላማቸው ጠንካራ የሚሏቸውን የአመራር አባላት በዚህም በዚያም በማጥቃት ድርጅትን ያዳከሙና የነዱ ይመስላቸዋል። ሀቁን ይክዳሉ እንጂ የድርጅቱ አመራር በየጊዜው ተቀይሯል። ድርጅቱ ሲመሰረት ከነበሩ የአመራር አባሎች የቀረሁት እኔ ብቻ ብሆንም ቢያንስ ለ 13 ዓመታት ከአመራር ወጥቼ ነበር። ዛሬ ያለው የድርጅቱ አመራር የ 41 ዓመቱ አይደለም -- በየጊዜውም ሲለዋወጥ የመጣ ነው። አልፎ ግን የድርጅቱን አመራር ሰያሚ አባላት ሲሆኑ ሌላው ምን አገባው ብንልም አግባብ ያለው ይሆናል። ድርጅቱ ግን ሊያፈርሱት የቃጡትንም፣ ሞት ለኢሕአፓ ብለው የጮሁትንም ምሕረት አድርጎ አቅፏቸው እንደነበር (እነሱ ግን ያደቆናቸው ሰይጣን ገደል እንደከተታቸው) የሚታወቅ ነው።

በኢህአፓነቴ በበኩሌ በጣም እኮራለሁ -- የዚህ ድርጅት አባል ባልሆን ኑሮ ሕይወቴ የባከነ ይሆን ነበር ብዬም አምናለሁ። የአጼውን ስርዓት ለመጣል በተደረገው ትግል መሳተፌም ያኮራኛል። ብዙዎች ሲያንቀላፉ የግንጠላ አቀንቃኞችን በመታገል የህዝብ እኩልነት ግን ይከበር ብለንም በመቆማችንም ተደሳች ነኝ። የባዕድን ወራሪዎችና በዳዮች ያኔም አሁንም መቃውሜና የድርጅቱን መስመር ማስከብሬም ተገቢ ነው ባይ ነኝ። ኢሕአፓ አንዴም ቢሆን ለድርጅታዊ ጥቅም ሲል የሀገርን ጥቅም አሳልፎ ባለመስጠቱ እንኳንስ ኢሕአፓ ሆንኩ እላላሁ። ይህን በተመለከተ ደግሞ ብዙ የምንለው ቢኖርም ጊዜውን ይጠብቅ ብዬ የማልፌው ነኝ። ምድረ አንጃና በታኝን፣ ከሃዲን ባንዳንም አምርረ መታገሌ የድርጅቴ ግዳጅ ነውና ዛሬም ነገም ብቅ የሚሉትን ከሀዲዎች አቅሜ እስከፈቀደ እታገላቸዋለሁ።

ዋናው ጉዳይ ግን የእኔ ታሪክና ማንነት በኢ.ሕ.አ.ፓ ትግልና ታሪክ የሚገለጽና የሚመዘን ነው። ትግልን የማያውቁ ትግል ማለት ድሎት ይመስላቸዋል። የኢ.ሕ.አ.ፓ ሁሉም ልጆች ግን መራራውን ትግል በቆራጥነት ተጋተሩትና መከራን ተቀብሉ እንጂ አልደላቸውም። ከነዚህ ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች ጋር ጎን በጎን መቆሜ ያስደስተኛል። ኢ.ሕ.አ.ፓን ያቋቋምነው ጥቂቶች ነበርን። ሆኖም ያን ለጊዜው ግዙፍ የነበረውን አገዛዝ ህዝብን አቅፈን እናቸንፈዋለን የሚል ጽኑ እምነት ነበረን። እንዳልነውም ጊዜ ቢፈጅም ቢያሰቃየንም አንኮታክተነዋል። ሽብር ያካሄደብንምን አረመኔ አገዛዝ ከሕዝብ ጋር ሆነን ታግለን ጥለነዋል-- ዛሬም ወያኔን እንደምንጥለው ጥርጥር የለንም። ሀገርና ሕዝብ ድል ሲነጠቁ ተስፋ ቆርጠን እጅ አልሰጠንም፤ ለባለ ነፍጥ አልሰገድንም፤ ለወያኔ ፈርመንና ተንበርክከን እንገዛ አላልንም። ድርጅታችን ሲጠቃና ሲጎዳ ታግለን አንሰራርተናል እንጂ ተስፋ ለቆረጠና ወኔው ለከዳው በታኝ ና አንጃ ሰለባ አልሆንም። ጀግና በመከራ ወርቅ በእሳት ይፈተናልና ከባድ ፈተናዎችን አልፈን ዛሬ ውር ውር የሚሉትን ኢ.ምንቶችንም ንቀን ዘግተናል። ትዕግስቱና ጽናቱ አለን፤ ተመክሮ፣ ሀቀና የሃገር ፍቅርም አለን። ጠላትና ቅጥረኞቹ ሁሉ ይበሳጫሉ ያራሉ እንጂ ፍንክች ንቅንቅ አንልም። አክራሪ ለሚሉንም "አዎ በሀገራችን ጉዳይ አክራሪ ነን!" እንላቸዋለን። በበኩሌ ከ17 አመቴ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ለተነሳ ትግልና ከዚያም ድርጅት ውስጥ ሆኜ መታገሌን ምንኛ ዕድለኛ ነኝ ያሰኘኛል። ዝርዝር ታሪክ ጊዜውን ይጠብቅ።

ረጅም ዕድሜና ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ እና ለኢ.ሕ.አ.ፓ!